የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፬
አዲስ አበባ ግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No 24.
ADDIS ABABA 15th May, 2007

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፳፩/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

የኢትዮጵያ ማኅበራዊ ተሃድሶ እና ልማት ፈንድን ለማፍረስ የወጣ አዋጅ ... ገጽ ፫ሺ፭፻፺፱

CONTENTS

Proclamation No. 521/2007

Ethiopian Social Rehabilitation and Development Fund Dissolution Proclamation Page 3599

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፳፩/፲፱፻፺፱

## የኢትዮጵያ ማኅበራዊ ተሃድሶ እና ልማት ፈንድን ለማፍረስ የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ማኅበራዊ ተሃድሶ እና ልማት ፈንድ የተቋቋመው ከአስቸኳይ የመልሶ ማቋቋምና ግንባታ ፕሮግራም ጋር የተያያዙ የማኅበራዊ ተሐድሶና ልማት ሥራዎችን ለመምራትና ለማስተባበር በመሆኑ፤

እነዚህ ሥራዎች ቀጣይ ቢሆኑም የመልሶ ማቋቋምና ግንባታ ፕሮግራምን አስፈላጊ ያደረገው አስቸኳይ ሁኔታ አሁን ስለሌለ እንደመደበኛ ተግባራቸው በሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አስፈፃሚ አካላት ሊካሄዱ ስለሚችሉ፤

የኢትዮጵያ ማኅበራዊ ተሃድሶ እና ልማት ፈንድ ሕልውና መቀጠል የሚያስከትለውን የሥራ ድግግም ለማስቀረት ይህንን ተቋም ማፍረስ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ማኅበራዊ ተሃድሶ እና ልማት ፈንድን ለማፍረስ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፭፻፳፩/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 521/2007.

## A PROCLAMATION TO PTOVIDE FOR THE DISSOLUTION OF THE ETHIOPIAN SOCIAL REHABILITAION AND DEVELOPMENT FUND

**WHEREAS,** the Ethiopian Social Rehabilitation and Development Fund was established to conduct and coordinate activities of social rehabilitation and development associated with the Emergency Recovery and Reconstruction Program;

**WHEREAS,** being continuous, these activities can be carried on as part of their regular duties by the appropriate executive organs of the Federal and or Regional Governments, now that the situation that had necessitated the launching of the Emergency Recovery and Reconstruction Program does not exist any longer;

**WHEREAS,** to forestall duplication of work that would result from the continued existence of the Ethiopian Social Rehabilitation and Development fund, it has been found necessary to dissolve this institution;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Ethiopian Social Rehabilitation and Development Fund Dissolution Proclamation No. 521/2007."

## ፪. <u>ስለ መፍረስ</u>

በአዋጅ ቁጥር ፲፱/፲፱፻፹፰ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ማኅበራዊ ተሃድሶ እና ልማት ፈንድ ፈርሷል።

## ፫. <u>የመብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ</u>

የኢትዮጵያ ማኅበራዊ ተሃድሶ እና ልማት ፈንድ መብቶችና ግዴታዎች ወደ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተላልፈዋል።

## ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## 2. Dissolution

The Ethiopian Social Rehabilitation and Development Fund which was established by Proclamation Number 19/1996 is hereby dissolved.

## 3. Transfer of Rights and Obligations

The Rights and obligations of the Ethiopian Social Rehabilitation and Development Fund have been transferred to the Ministry of Finance and Economic Development.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall enter into force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 15th day of May, 2007**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**